# የ ፩ኛ ና ፪ኛ

# ጴጥሮስ መልዕክት

# ጥናት

*“በቅዱሳን ነቢያትም ቀድሞ*
*የተባለውን ቃል*
*በሐዋሪያቶቻችችሁም ያገኛችኋትን*
*የጌታንና የመድኃኒትን ትእዛዝ*
*እንድታስቡ በሁለቱ*
*እያሳሰብኋችሁ ቅን ልቡናችሁን*
*አነቃቃለሁ።”*

**2ጴጥ. 3፥2**

# ማውጫ

ገጽ


1. መግቢያ፡- . . . . . . . . . . . . . . . . .
2. “ውብ ርስት”፡- . . . . . . . . . . . .
3. “የእምነት መፈተን”፡- . . . . .. . . . . . . . .
4. “በኑሯችሁ ምሰሉት”፡- . . . . . . . . . . . .
5. “ህያው ትውልድ”፡- . . . . . . . . . . . . . .
6. “የአማኝ ተግባር”፡- . . . . . . . . . . . . . .
7. “የባልና የሚስት አደራ”፡- . . . . . . . . . .

8. “ምሳሌያዊ ሕይወት”፡- . .. . . . . . . . . . . .
9. “ለእግዚአብሔር መኖር”፡- . . . . . . . . . . .
10. “መገዛት”፡- . . . . . . . . . . . . . . . .
11. “የፍሬያማ ሕይወት ምሥጢር”፡- . . . . . . .
12. “የምታምነውን እወቅ”፡- . . . . . . . . . . .

13. “ነፃነትህን ጠብቅ”፡- . . . . . . . . . . . . .
14. “ተግቶ መጠበቅ”፡- . . . . . . . . . . . .

# *የጴጥሮስ መልዕክት*

## *መግቢያ*

የጴጥሮስ መልዕክት ለመንጋው በሚጠነቀቅ መጋቢ የተጻፈ የማበረታቻ መልዕክት ነው። ይህ መልዕክት በማያምን ኅብረተሰብ ውስጥ አማኞች ጌታን እያስከበሩ እንደ ብርሃን ልጆች ይኖሩ ዘንድ መለየታቸውን ያሳያል።

### *ጸሐፊው ማን ነው?*

የጴጥሮስ መልዕክት ጸሐፊ ማንነት በአንዳንዶች ዘንድ አጠያያቂ ቢሆንም፤ በሁለቱም መልዕክቶች ላይ ጸሐፊው ራሱን ሐዋሪያ ጴጥሮስ በማለት ገልጿል።

አንዳንዶች ግን መልዕክቱን ሐዋርያው ጴጥሮስ ሳይሆን ሌላ ሰው በእርሱ ስም እንደ ጻፈው አድርገው ያስተምራሉ።

ለዚህ የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ምክንያት መልዕክቱ የተጻፈበት የአጻጻፍ ስልት ጴጥሮስ ነበረው ብለው ከሚገምቱት የቋንቋ ችሎታ ጋር የሚመጣጠን አለመሆኑ ነው። ከዚህ የተነሳ ጸሐፊው ጴጥሮስ ሊሆን አይችልም በማለት ይደመድማሉ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በመጽሐፉ የተጠቀሰው የበረታ ስደት ሐዋርያው ጴጥሮስ ከሞተ በኋላ እንጂ እርሱ በሕይወት በነበረበት ዘመን የነበረን ስደት የሚያሳይ አይደለም የሚል ምክንያት ነው። በነዚህ ሁለት ምክንያቶቹን ሐዋርያው ጴጥሮስ የመልዕክቱ ጸሐፊ አይደለም ይላሉ።

ከላይ የተሰጡት ምክንያቶች በግምቶችና በግል መረዳቶች ላይ የተመረኮዙ ስለሆኑ፤ ከነዚህ ምክንያቶች ይልቅ በሁለቱም መልዕክቶቹ ላይ ጸሐፊው ሐዋርያው ጴጥሮስ መሆኑን ስለሚያመለክት ያንኑ መውሰድ መልካምና ትክክለኛም ነው።

### *የመልዕክቱ አጠቃላይ ሀሳብ*

የጴጥሮስ መልዕክት ቅዱሳንን ሊያሳዩት ስለሚገባ የሕይወት ውበት፥ በተሰማሩበት መስክ ስለሚጠበቅባቸው ኃላፊነት፥ ስለመከራ ወይም ስደት እውነንነት፥ ስለ አላቸው የርስት ተስፋና በምድር የእንግድነት ኑሯቸው እንዴት መመላለስ እንዳለባቸው የሚያስተምር፤ ለተግባራዊ ምላሽ የሚያነቃቃ መጽሐፍ ነው።

### *የ፩ኛ ጴጥሮስ አበይት ሀሳቦች*

በአንደኛ ጴጥሮስ ውስጥ አማኞች ከአገኙት ድነት የተነሳ በእንዴት ዓይነት ሕይወት መመራት እንዳለበቸው ያስተምራል። መልዕክቱን በአራት ዋና ዋና ክፍል ከፍለን መመልከት እንችላለን።

፩ኛ. *ቅዱሳን ድነታቸው ድንቅ የተጠበቀላቸው ርስትም ውብ ነው።* (1፡1-12)

ሐዋርያው ለቅዱሳን ስለተሰጠው ታላቅ ድነት ጌታን እየባረከ፥ ይህ ድነት የማያልፍ ርስትን እንዳቀዳጃቸው ይናገራል (1፡3-5)። እነዚህ ቅዱሳን ከእምነታቸው የተነሳ የሚያልፉበት ሰልፍ ለጊዜው ያሳዘናቸው ናቸው። ኋላ ግን የሚወዱትን ጌታ ሲያዩት ክብር በሞላበት ታላቅ ደስታ እንደሚደሰቱ ይገልጽላቸዋል (1፡ 6-9)።

ይህ ድንቅ ጥሪ ነብያት ተግተው የፈለጉት፥ መላእክት የተመኙት ነው በማለትም የተበተኑ መጻተኞችን ያነቃቃል። (1፥10-12)

**፪ኛ. በክርስቶስ የተገኘ ድነት ጽድቅና ፍቅር የሚታይበት ህይወት ነው። (1፥13-2፥3)**

በክርስቶስ የተገኘው ድነት ቅዱስ የሆነውን የሰማይ አባትን በመምሰል የቅድስና ሕይወት የሚጠበቅበት አዲስ ጉዞ ነው። (1፥13-17)

ይህ የጽድቅ ኑሮ የከበረ ዋጋ የተከፈለበት ስለሆነ (1፥18-21) የዚህ ድንቅ ሕይወት ተካፋይ የሆኑ ከቀድሞ ኑሮአቸው በመለየት ለፍቅር ራሳቸውን እንዲሰጡ ይመክራል። (1፥22)

ከቀደመው ሕይወት በመለየት በጽድቅና በፍቅር ለመመላለስ ደግሞ ጉልበት የሚሆንን የእግዚአብሔር ቃልን መመገብና መለማመድ እንዳለባቸውም ያሳስባል (1፥23-25, 2፥1-3)።

***፫ኛ. በክርስቶስ የዳኑ ለመንፈሳዊ ቤትነትና የክህነት አገልግሎት ተለይተዋል።***

አማኞች እግዚአብሔር ለአለው የተቀደሰ ዓላማ የተለዩ ናቸው። ሁሉም መንፈሳዊ ቤትና ካህናት ለመሆንም የተጠሩ ናቸው። (2፥4-12)

***፬ኛ. አማኝ እግዚአብሔር ለደነገገው የሥልጣንና የቤተሰብ ሥርዓት መገዛት ይጠበቅበታል።***

ሐዋርያው ለባለሥልጣኖች መገዛትና መታዘዝ ተገቢና አደራም አልፎም ጌታን መታዘዝ ነው፤ የሚል ትምህርትን ይሰጣል።

በትዳር ጓደኞች መካከል ሚስት ለባሏ እንድትገዛና ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ ውበት እንዲኖራት ሲመክር፥ ባል ደግሞ ሚስቱን እንዲያከብር ያዛል።

በአጠቃላይ እርስ በርስ በፍቅርና በመተሳሰብ በቤት ውስጥ መኖር ተገቢ መሆኑን ይገልጻል።

***፭ኛ. አማኝ በምድር ሳለ መከራ ሊገጥመው ይችላል።***

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መመላለስ ከመከራ ነጻ አያደርግም። እንዲያውም እንደ ፈቃዱ እየተመላለሱ በግፍ መከራን መቀበል ሊኖር ይችላል። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ሐዋርያው ቅዱሳን ለሥሙ በሚነቀፉበት ወቅት ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ እንዲሰጡ እየመከረ በዚህ ውስጥ ለሚያልፉ ስላለ ብድራትም ይናገራል።

አማኞች የክርስቶስን ፈለግ እየተከተሉ በመከራ ውስጥ ቢያልፉ፤ እፍጻሜ ላይ ታላቅ ክብርን ሊቀበሉ እንዳለም ያስገነዝባል (3፥13-4፥19)።

***፮ኛ. በቅዱሳን አንድነት ውስጥ መልካም አገዛዝና ትህትና ሊኖር ይገባል።***

በመጨረሻው ምዕራፍ በቤተክርስቲያን መሪዎችና በምዕመናን መካከል ሊኖር ስለሚገባ መንፈስ ሐዋርያው ጥበብ የተሞላበትን ምክር ይሰጣል።

ሽማግሌዎች እረኞች ስለሆኑ መንጋውን በመልካም መንፈስና ልብ ሊመሩት እንደሚገባ በመናገር፤ መንጋው ደግሞ ትሁታንን ከፍ የሚያደርግና ጸጋን የሚሰጥ ጌታ ስላለ በትህትና ለመሪዎቻቸው እንዲገዙ ያሳስባል።

በመጨረሻም ሽማግሌዎችና መንጋው ሙሉ በሙሉ በጌታ ላይ እንዲደገፉ፤ በሰይጣን አሳች አሠራርና ምክሩ እንዳይጠለፉም ይጠነቀቁ ዘንድ ይመክራል። በ5፡1-11

በማጠቃለያም ሐዋርያው የመዝጊያ ሰላምታን በማቅረብ ጌታን በማክበር መልዕክቱን ያጠቃልላል።

## የ፪ኛ ጴጥሮስ አበይት ሀሳቦች

በሁለተኛው መልዕክቱ ሐዋርያው አማኞች ስለተጠሩበት ድንቅ ሕይወት፥ በዚህ ህይወት ጉዞአቸው ከእውነት ሊያወጣቸው ስላለ ትምህርትና ስለ መጨረሻው ዘመን ጽፏል።

እግዚአብሔርን እየመሰሉ ለመኖር የሚያስፈልግ ነገር ሁሉ ተሰጥቷል። ይህን ተገን አድርጎ በትጋት መራመድ የአማኞች አደራ ነው። (1፡1-14) አማኝ የሚለማመደው ሕይወት ተረት ያልሆነና በጸና የትንቢት ቃል የተረጋገጠ እውነት ነው። (1፡15-21)

ጸሐፊው እንደዚህ የጸናን እውነት የሚያጣምሙ ሀሰተኞች ስላሉ፤ አማኞች ራሳቸውን ከኑፋቄ ትምህርት እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃል። በመቀጠልም የነዚህ አስተማሪዎች ባህርይና በፍጻሜ ላይ ስለሚጠብቃቸው ፍርድም ይናገራል። (2፡1-22)

በሶስተኛ ደረጃ መልዕክቱን የጻፈበትን አላማ ሲገልጽ “. . . የጌታንና የመድኃኒትን ትእዛዝ እንድታስቡ . . . ቅን ልቡናችሁን አነቃቃለሁ” ይላል። በመቀጠል ዘባቾች በመጨረሻው ዘመን እንደሚነሱ በመግለጥ፥ አማኞችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በትጋት እንዲጠብቁና ከሚገለጠው ቁጣ እንዲያመልጡ ይመክራል። (3፡1-10)

ይህን ጌታ የሚጠባበቁ ራሳቸውን ያለ ነውርና ያለነቀፋ ለመጠበቅ እንዲተጉና በክርስቶስ ጸጋ እውቀት እንዲያድጉ በማሳሰብ መልዕክቱን ይደመድማል። (3፡11-18)

## ማጠቃለያ

የሚከተሉት ሦስት ሀሳቦች ሐዋርያው በሁለቱ መልእክቶቹ ያስተላለፈውን ጽንሰ ሀሳብ ጠቅለል ያደርጉልናል።

1ኛ. ክርስትና የጌታ ስጦታና በእርሱም አጋዥነት የሚኖርበት ሕይወት ነው።

2ኛ. በዘመን ፍጻሜ ሀሰተኞችንና ሀሰተኛ ትምህርታቸውን መለየትና ከትምህርታቸው መጠንቀቅ ይገባል።

3ኛ. የክርስቶስን መመለስ ተግቶ መጠበቅና የመዘግየቱ ምክንያት ሌሎች ይድኑ ዘንድ መሆኑን በመረዳት ይህን ለማፋጠን መንሳሳት ይገባል።

<u>የመልዕክቶቹ አስተዋጽኦ</u>

## የ፩ ጴጥሮስ መልዕክት ይዘት

1. በክርስቶስ የተጠሩለት ሕይወት (1፥1-2፥10)
    - የርስት ተስፋ አለው (1፥1-12)
    - ይህ ሕይወት የቅድስና እና የፍቅር ሕይወት ነው 1፥13-25
    - የሚያድግ፥ እንደ ህንጻ የሚሰራና የክህነት ሕይወት ነው። 2፥1-10

     ስለዚህ
        - ዝግጅትን ይጠይቃል
        - ዋጋን ያስከፍላል
        - ተግባራዊ ምላሽን ይጠይቃል
2. የክርስትና ሕይወት መገለጫዎች 2፥12--3፥7
    - እንደ ጥሩ ምስክር 2፥12
    - እንደ ጥሩ ዜጋ 2፥13-17
    - እንደ ጥሩ አገልጋይ 2፥18-25
    - እንደ መልካም የቤተሰብ አባል 3፥1-7
3. ክርስትናን በተለያዩ ሁኔታዎች 3፥8 – 5፥11
    - በጥሩ ልብና በንጹህ ኅሊና 3፥8-22
    - በስደት ውስጥ 4፥1-2
    - እንደ ክርስቶስ መኖር 4፥1-19
        - በባህርያችን
        - በአገልግሎታችን
        - በእምነታችን
4. እርስ በርሳችን ስለሚኖረን አደራ 5፥1-11
    - እርስ በርስ መቀባበል ሽማግሌዎች፥ ወጣቶች
    - በትህትና ራስን ለኃይለኛው እግዚአብሔር ማስገዛት
5. ማጠቃለያ 5፥12-14

## የ፪ኛ ጴጥሮስ መልዕክት ይዘት

1. በእግዚአብሔር ለተጠሩለት ሕይወት መትጋት 1፥3-11
    - አስፈላጊው ሁሉ ተሰጥቷል 1፥1-3
    - ተስፋ ያለው ሕይወት ነው 1፥4
    - ለሚተጉ ፍሬ አለ 1፥5-11
2. የክርስትና ባህርይ እንደ እግዚአብሔር ቃል 1፥12-21
    - ህያውን ቃል ማጥናት 1፥12-15
    - የህያው ቃል ክብር 1፥16-18
    - የህያው ቃል ትርጉም/ ጥቅም 1፥19-21
3. ክርስትናና የሀሰት ትምህርት 2፥1-
    - ከሀሰት ነጻ የወጣ ሕይወት 2፥1-9
    - የሀሰተኞች ባህርይ 2፥10-12
    - ሀሰተኞች ለጥፋት ተጠብቀዋል 2፥12--22
4. ክርስትና ተስፋ ያለው ሕይወት ነው 3፥1-18
    - የመልዕክቱ ዓላማ (ማነቃቃት) 3፥1-2
    - ዘባቾችና የጌታ መመለስ 3፥3-7
    - የጌታ መዘግየት ዓላማ 3፥8-9
    - በርግጥ ይመለሳል 3፥10-13

- ያለ ነቀፋ ለመገኘት ትጋ 3፥14-16

## ጥናት አንድ

### “ውብ ርስት”
### 1ኛ ጴጥሮስ 1፥1-5

*መግቢያ፡-* ይህ ክፍል ጴጥሮስንና የመልዕክቱን ተቀባዮች ካስተዋወቀ በኋላ ቅዱሳኑን ስለተቀዳጁት ታላቅ ድነትና ስለ ተጠበቀላቸው ድንቅ ርስት ይናገራል።

*ዓላማ፡-* ድንቅ ሰለሆነው ድነታችንና ስለተዘጋጀልን ርስት ጌታን መባረክ እንዳለብን ማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁጥር 1 መሠረት ደብዳቤውን የጻፈው ማነው?
2. ደብዳቤው በየት ሥፍራ ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች ነው የተጻፈው?
3. ደብዳቤው ስለተጻፈላቸው ሰዎች ማንነት በቁጥር ሁለት የተጠቀሰውን በመዘርዘር ተወያዩበት።
   <u>ለመሪው፡-</u>
   - እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ ያወቃቸው
   - በመንፈስ ቅዱስ የተቀደሱ
   - በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተረጩ
4. በቁጥር ሁለት ደህንነታችንን አስመልክቶ ስለአብ፥ መንፈስ ቅዱስ እና ጌታ ኢየሱስ ሥራ ምን ያስገነዝባል?
5. “ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ” የሚለው ሰላምታ ምን ትርጉም ይሰጣል? እያንዳንዱን ቃላት በመተንተን ትርጉሙን ተወያዩበት።
6. ከቁጥር 3-5 ጴጥሮስ እግዚአብሔርን በባረከበት ባርኮት ላይ በመመርኮዝ፡-
   ሀ. የእግዚአብሔር የማዳን ዓላማ ምን ነበር?
   ለ. በምን አማካይነት ነው የዳኑት?
   ሐ. እንዴት ነው የዳኑት?
   መ. ምንን ለመቀበልስ ነው የዳኑት?
7. ደህንነት የተገኘው ከምን የተነሳ ነው? ይህስ የሚገልጸው ምንድን ነው?
8. በክፍሉ የተገለጠው ርስት፤
   - ለነማን ቀርቶአል?
   - እስከ መቼ? ይህስ በየት ቀርቶላቸዋል? ይህን ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - እስከዚያ ድረስ እንዴት ነው የተጠበቁት?

### ማዛመድ

1. ደህንነትህን በተመለከተ እግዚአብሔርን ስለመባረክ የተገነዘብከውን ለቡድንህ አካፍል።
2. ለሰማይ ርስት አሁን እየተጠበቅህ መሆኑ ለምታልፍባቸው ሁኔታዎች የሚሰጥህ ተስፋ/ጽናት ምንድን ነው?

የሚጠና ጥቅስ 1ኛ ጴጥ. 1፥3-5

## ጥናት ሁለት

### "የእምነት መፈተን"
### 1ኛ ጴጥ. 1፡6-12

**መግቢያ፡-** በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጴጥሮስ በተለያዩ ፈተናዎች እያለፉ ለነበሩት ቅዱሳን የሰጠውን ማበረታቻ እንመለከታለን።

**ዓላማ፡-** የእምነት መፈተን ክብርን ስለሚያመጣ በምንፈተንበት ወቅት ሊኖረን ስለሚገባ አቋም ግንዛቤን ለመስጠት።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ምንባቡ "በዚህም" በሚል ቃል መጀመሩ ምንን ያመለክታል? ካለፈው ጥናት ጋር በማገናዘብ ተወያዩበት።
2. በቁጥር 6-7
   - "ቅዱሳን ደስ ይላችኋል እና አዝናችኋል" የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው?
   - እነዚህ በአንድነት በአማኞች ሕይወት ውስጥ መኖራቸው ስለክርስትና ሕይወት ምን ያመለክታል?
3. በቁጥር 7 የተለያዩ ፈተናዎች ወደ ክርስቲያኖች ሕይወት ስለመምጣቱ የተሰጠው ምክንያት ምንድን ነው? ተወያዩበት።
4. የእምነት መፈተን ከምን ጋር ነው የተነጻጸረው? ይህስ ምን ያመለክታል?
5. በምንባቡ መሰረት የተፈተነ እምነት ፍሬ ምንድን ነው? እንዴት ትረዳዋለህ?
   ለመሪው፡- ምስጋና፥ ክብር እና ውዳሴ ማፍራት።
6. በቁጥር 8 "እርሱንም" ተብሎ የተጠቀሰው ማነው? በእርሱና በቅዱሳኑ መካከል ስላለው ግንኙነት የተገለጸውን ተወያዩበት።
7. "የእምነታችሁ ፍጻሜ እርሱም የነፍሳችሁን መዳን እየተቀበላችሁ" የሚለው ሀረግ ፍቺ ምን እንደሆነ በማብራራት ግለጽ።
8. በቁጥር 10-11 ነብያት ተብለው የተጠሩት እነማን ናቸው?
9. እነዚህ ነብያት ስለምን ይናገሩና ይመረምሩ ነበር?
10. ከቁጥር 10 እስከ 12 ስለድነት ታላቅነት፥ ስለአሁኑ ዘመን ክብር የተገለጸውን ተወያዩበት።
11. ይህንን ድነት መላዕክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ የሚለው ምንን ለመግለጽ ነው?

### ማዛመድ

1. በዚህ ክፍል ጌታ ያስተማረህን አዲስ ነገር ለቡድንህ አካፍል።
2. በጌታ ፍቃድ የምታልፍባቸው ፈተናዎች ለእምነትህ ጥራት የሚያመጡና መጨረሻቸውም መልካም ነው። ይህ ግንዛቤ ለሕይወትህ እንዴት እንደሚጠቅምህ ግለጽ።

የሚጠና ጥቅስ 1ኛ ጴጥ. 1፡6-7

## ጥናት ሦስት

## “በኑሯችሁ ምሰሉት”

1ኛ ጴጥ.1፥13-25

*መግቢያ፡-* በዛሬው ጥናታችን በከበረው ደም የተዋጁና ከማይጠፋ ዘር የተወለዱ የዋጃቸውን ጌታ ባህርይ በሚያሳይና እርስ በርስ ደግሞ ፍቅር የተሞላበት ኑሮ ይኖሩ ዘንድ የተሰጣቸውን ምክር እናጠናለን።

*ዓላማ፡-* ጽድቅና ፍቅር የተሞላበትን ሕይወት እንድንኖር በከበረው ደም መዋጀታችንን ማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁጥር 13 “ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ” የሚላቸው ስለምንድን ነው? በእንዴት ያለ ሁኔታ ሊሆኑ ይገባል? በምን ወቅት ነው የሚያገኙትስ?
2. በቁጥር 14 አትከተሉ ብሎ የሚነግራቸውን ግለጽ።
3. በቁጥር 15-16 ቅድስናን አስመልክቶ እንደ ማንና በምን ሁሉ ነው ተቀደሱ የሚለው?
4. በቁጥር 17
   - በፍርሃት ኑሩ የሚላቸው ከምን የተነሳ ነው? በምን ወቅት?
   - “በፍርሃት ኑሩ” የሚለው አባባልን በምንባቡ መሰረት እንዴት ትረዳዋለህ?
5. በቁጥር 18-19 ኑሯቸውን አስመልክቶ የሚነግራቸው ምንድን ነው?

   *ለመሪው፡-*
   - ከአባቶቻቸው እንደወረሱት ያለ ኑሮ አይደለም
   - በምድር ንብረት የማይለካ መሆኑን (በብርና በወርቅ ያይደለ)
   - በክቡር የክርስቶስ ደም የተገኘ መሆኑን
6. ከቁጥር 13-19 በመደጋገም የተጠቀሰው ቃል ምንድን ነው? በቃሉ ዙሪያ ያሉትን ሀሳቦች በዝርዝር ተመልከታቸው።

   *ለመሪው፡-*
   - ተስፋ ስላለ በትጋት መኖር ይገባል (ቁ. 13)
   - የዐመፅ ምኞትን ከመከተል በመቆጠብ መኖር (14)
   - የጠራንን ባህርይ የሚያሳይ ኑሮ መኖር (15-16)
   - ፍርድ እንዳለ በመገንዘብ መኖር (17)
   - መኖራችን (ሕይወታችን) የከበረ ነገር የተከፈለበት ስለሆነ ልናቃልለው አይገባም (18-19)
7. በቁጥር 20-21 መሰረት
   - “ዓለም ሳይፈጠር የታወቀ” እና “በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ” የሚለው ስለምንድን ነው?
   - በነዚህ ቁጥሮች ስለ ቅዱሳን፥ ስለጌታ የተገለጸው ምንድን ነው?
8. በቁጥር 22 ስለመዋደድ የተዘረዘረው ምንድን ነው? እንዴትስ ነው መዋደድ ያለብን?
9. በቁጥር 23 ከምን ተወለዳችሁ ይላል? ስለዚህ ዘር ምንድን ነው የተጠቀሰው?

10.በቁጥር 24-25 ስለእግዚአብሔር ቃል የተጠቀሰው ምንድን ነው?

ማዛመድ

1. ከዛሬው ጥናት በዕለት ኑሮህ ልታሳየው ስለሚገባ የጽድቅ ሕይወት የተማርከውን ለቡድንህ አካፍል።
2. ስለወንድማማች መዋደድ ምን ተማርክ? ልትወስድ የወሰንከውን እርምጃ ለቡድንህ አካፍል። ለዚህ ውሳኔ ከወገኖችህ ምን ዓይነት እገዛ ያስፈልግሃል?

የሚጠና ጥቅስ 1ኛ ጴጥ. 1፥15-16

## ጥናት አራት

## "ህያው ትውልድ"
## 1ኛ ጴጥ. 2፥1-10

*መግቢያ፡-* በዚህ ክፍል ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት መፈለግ እንዳለባቸውና ወደ ክርስቶስ ቀርበው መልካም መንፈሳዊ ቤት ሆነው መሠራት እንዳለባቸው የተጻፈውን እንመለከታለን።

*ዓላማ፡-* የቅዱሳን ሕይወት የማደግ፤ የመሠራትና የካህንነት ሕይወት መሆኑን ማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. 1-3 በመመልከት
   ሀ. ጸሐፊው ቅዱሳንን ምን እንዲያስወግዱ ነው የሚመክራቸው?
   ለ. የሚያስወግዱበት ምክንያት ምንድን ነው?
   ሐ. ምን እንዲመኙ ይመክራቸዋል?
   መ. እንዴት እንደሚመኙ ነው የሚመክራቸው?
   - ተንኰል የሌለበት ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - የቃሉ ወተት የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው?
2. በቁጥር 4 ወዴት እንዲቀርቡ ነው የሚመክራቸው? በዝርዝር

   ተወያዩበት
3. በቁጥር አምስት የመቅረብና የመሠራት ውጤት ምንድን ነው?
   ሀ. ለመሰራት ከቅዱሳን ምን የሚጠበቅ ይመስልሃል?
   ለ. ለመሠራትስ ምን ማድረግ አለባቸው?
4. በቁጥር 6 የተነገረው ትንቢት ምንድን ነው? ከቁጥር 4 ጋር ምን ግንኙነት አለው?
5. ከ7-8 ይህ ድንጋይ የሚፈጥረው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?
6. በቁጥር 8 ላይ ተሰናከሉ ሲል ምን ማለት ነው? "ግንበኞች" የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ የሚለው ሀረግ ምን ያመለክታል?
7. ከቁጥር 9-10 ባለው፡-
   - የተጠሩት ከየት ወደ የት ነው?
   - የመጠራታቸው ዓላማስ ምንድን ነው?
   - ስለእነርሱ የተነገረ አራት ነጥቦች ምን ምን ናቸው?/ ምንንስ ያመለክታሉ?
   - የአለፈውንና የአሁን ሁኔታዎችን አስመልክቶ የተገለጠው ምንድን ነው?
   - ይህስ ምንን ያመለክታል?

ማዛመድ

1. በሕይወት ልትመኝ ስለሚገባህና ልታስወግድ ስለሚገባህ ነገር ምን ተማርክ? ይህስ በሕይወትህ ምን ያህል ይታያል?

2. ሕይወታችን ከተመሰለበት ነገርና ለመሠራት ስላለህ ኃላፊነትና ድርሻ የተረዳህውን አካፍል።
3. የእግዚአብሔርን ድንቅ የሆነ አጠራርን ዓላማ ስታስብ፤ አሁን የተሰጠህን ኃላፊነት እንዴት እንድትወጣው ያነሳሳሃል?

**የሚጠና ጥቅስ 1ኛ ጴጥ. 2፥2-3፤ ወይም 2፥9-10**

## ጥናት አምስት

## “የአማኝ ተግባር”
## 1ጴጥ. 2፥11-23

*መግቢያ፡-* የዛሬው ጥናታችን ቅዱሳን በማያምኑ ዘንድ እንዴት መኖር እንዳለባቸውና በስልጣን ላይ ላሉ መገዛት ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ያስተምራል። እንደ ፈቃዱ እየተመላለሱ ሊደርሱባቸው ስለሚችሉ የመከራ አይነቶችና በዚያም ውስጥ ሊከተሉት ስለሚገባቸው ፈለግ የሰጣቸውን መመሪያ እንመለከታለን።

ዓላማ፡- በፈቃዱ ውስጥ ስንሆን ለበላዮች መገዛት እንዳለብንና በዛም ውስጥ መከራም ሊደርስብን እንደሚችል ለማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁጥር 11-12ን በመመልከት
   - የሚለምናቸው ስለምንድን ነው?
   - ከምንድን እንዲርቁ ነው የተጠየቁት? ለምንስ?
   - መልካም ኑሮ የሚያመጣው ውጤት ምንድን ነው?
   - አህዛብ መልካም ኑሮአቸውን የሚያውቁት መቼ ነው?
2. ከ 13-14 መሠረት፡-
   - ለማን እንዲገዙ ይመክራቸዋል? ለምን?
   - የሚገዙበት ምክንያት ምንድን ነው?
   - የባለስልጣኖች ተግባርስ ምንድን ነው?
3. በቁጥር 15 መሠረት የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን ማለት እንደሆነ ተነጋገሩበት።
4. በቁጥር 16 መሠረት አርነታቸው እንዴት እንዲገለጽ ነው የሚመክራቸው?
5. በቁጥር 17 የተሰጣቸው ትእዛዝ ምንድን ነው? ምንስ ያሳያል?
6. በቁጥር 18 ላይ
   - የተሰጠው ምክር ለማን ነው?
   - ለነማን እንዲገዙ ነው የተመከሩት?
   - ይህስ ምን ያሳያል?
7. በቁጥር 19-20 መሠረት
   - ምስጋና የሚያመጣ መከራ የቱ ነው?
   - በግፍ መከራን የሚቀበል ሊያስብ የሚገባው ምንድን ነው?
   - በክፍሉ መሠረት ሁለቱን መከራ እንዴት እንለያለን?
8. በቁጥር 21-25 መሠረት
   - የተጠሩት ለምንድን ነው?
   - ቅዱሳን
     ሀ. የማንን ፈለግ ነው የሚከተሉት?
     ለ. እርሱ በመከራ ሲያልፍ ያደረገውና ያላደረገው ምንድን ነው?
     ሐ. ይሄንን ሁሉ ያደረገው ለማን ነው?

መ. ያደረገበትስ ምክንያት?
ሠ. ፍሬውስ ምንድን ነው?

9. “ለኃጢያት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር” ሲል ምን ማለቱ ነው?

## ማዛመድ

1. ከዛሬው ጥናት አማኞች እግዚአብሔርን እንደሚያከብሩ አንተስ ምን ማድረግ እንደሚገባህ ተማርክ።
2. ለበላዮች ስለመገዛት ምን ተማርክ? በሕይወትህ ይህስ ምን ያህል ይታያል?
3. በመከራ ስታልፍ ጠንቅቀህ ማወቅ ስላለብህ የተረዳህውን ለቡድንህ አካፍል።

የሚጠና ጥቅስ 1ኛ ጴጥ. 2።24-25

## ጥናት ስድስት

# “የባልና የሚስት አደራ”

## 1ጴጥ. 3፤1-7

**መግቢያ፡-** በዛሬው ጥናት ባልና ሚስት በትዳራቸው ውስጥ እርስ በርሳቸው እንዴት ሊቀባበሉ እንደሚገባ የተሰጠውን ምክር እንመለከታለን። ከዚህ ምክር ውጪ መራመድ ስለሚያስከትለው ችግርም የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ እናያለን።

በተጨማሪም በትዳር ውስጥ ሊኖር ስለሚገባ መከባበርና ስለ እውነተኛ ውበት የተሰጠውን ምሳሌ እንመለከታለን።

**ዓላማ፡-** የሚስቶች የውስጥ ውበትና የባሎች ሚስቶችን የማክበር ሕይወት የሚያፈራው ፍሬ እንዳለ ማስገንዘብ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁጥር 1 እና 2 መሠረት
   - ሚስቶች ምን እንዲያሳዩና እንዲያደርጉ ነው የሚመከራቸው?
   - ለምን አይነት ባሎች? ፍሬውስ ምንድን ነው?
2. ቁጥር 3-6 በመመልከት
   - ውበታቸው በምን እንዲገለጽ ይመከራቸዋል?
   - “የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ” የሚለው ሀረግ ምን ያመለክታል?
   - የተሰጡት ምሳሌዎች እነማን ናቸው?
   - የሣራ ውበት የተገለፀው እንዴት ነው?
   - ሚስቶች የሣራ ልጆች መሆናቸው የሚገለጠው እንዴት ነው?
3. ቁጥር ሰባትን በመመልከት
   - ለባሎች የተሰጠው ምክር ምንድን ነው?
   - “ደካሞች” ሲል ምን ማለት ነው?
   - እንዴት አክበሯቸው ነው የሚለው?
   - ሚስቶችን ያለማክበር ምን ያስከትላል?

## ማዛመድ

1. ስለ እውነተኛ ውበት ከዚህ ምንባብ ምን ተማርክ? ይህንስ ውበት ለመጠበቅ ምን ማድረግ ያለብህ ይመስልሃል?
2. አንዱ የአንዱን ድካም ለመፍረድ ሳይሆን ድካሙን አይቶ ስለመረዳዳትስ ምን ተማርክ?
3. ጸሎትህ ሊሰማልህ ከፈልግህ ምንን ማስወገድ እንዳለብህ ከክፍሉ ተገንዘብህ?
4. በትዳር ውስጥ ካላችሁ በዚህ ምንባብ ካለው ትምህርት አንጻር ራሳችሁን እንዴት አያችሁት?

የሚጠና ጥቅስ 1ኛ ጴጥ. 3፥3-4፥ 3፥7

## ጥናት ሰባት

## "ምሳሌያዊ ሕይወት"
## 1ጴጥ. 3፥8-22

***መግቢያ፡-*** የክርስቶስን ፈለግ በመከተል ቅዱሳን ከሌሎች ጋር እንዴት መኖር እንዳለባቸውና በክፉ ፈንታ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የተጻፈውን እንመለከታለን።

***ዓላማ፡-*** እንደ ክርስቶስ በሚጐዳን ነገር ውስጥ እንኳን ከሌሎች ጋር በፍቅርና በሰላም መኖር እንዳለብን ለማስገንዘብ።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በቁጥር 8 እና 9 *መሠረት* በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ሕይወታቸውን እንዲመሩ ይነግራቸዋል?
2. በቁጥር 10-11 *መሠረት* ሰው ሕይወትን የሚወድና መልካም ቀንን ለማየት የሚፈልግ ምን እንዲያደርግ ነው የተዘረዘረው?
3. በቁጥር 12 ስለምንድን ነው የሚናገረው? ከቁጥር 11 ጋር እንዴት ይያያዛል?
4. በቁጥር 13-14 *መሠረት* የሚጠይቃቸውና የሚመክራቸው ስለምንድን ነው?
5. በቁጥር 15 የተሰጣቸው ሁለት ምክር ምንድን ነው? በእንዴት ያለ መንፈስ?
6. በቁጥር 16 *መሰረት* ቅዱሳን ስለሚታሙበት የተጠቀሰው ምንድን ነው? ስለ ምላሻቸው ምን ተጠቅሶል? ለምን?
7. በቁጥር 17-18
    - የተሻለ ብሎ የሚመክራቸው ስለምንድን ነው?
    - የተሰጠውስ ምሳሌ ማነው?
    - እርሱ ያደረገውና በሕይወቱ የተፈጠረውስ?
8. ቁጥር 19-22
    - ክርስቶስ ምን አደረገ?
    - በቁጥር 20 ስለ እግዚአብሔር የተገለጠ ምንድን ነው?
    - የተሰጠው ምሳሌ ምንድን ነው?
    - የምሳሌው አስፈላጊነት ምንን ለመግለጽ ነው?
    - ድል ስለነሳው ጌታ የተሰጠው መግለጫ ምንድን ነው? (22)

### *ማዛመድ*

1. *መልካም* ቀንና ሕይወትን የምትወድ ከሆነ ልታደርግ ስለሚገባህ ነገር ምን ተረዳህ?
2. ከዛሬው ጥናት ከሌሎች ጋር ስትኖር ክፉ እንኳን ቢደርስብህ ምን እንድታደርግ ተማርክ?

3. በመከራ ውስጥ ስታልፍ ምሳሌ ከሆነህ ጌታ ስለ መከራ ምን አዲስ ነገር ትማራለህ?

የሚጠና ጥቅስ 1ኛ ጴጥ. 3፥10-12

## ጥናት ስምንት

## “ለእግዚአብሔር መኖር”

## 1ጴጥ. 4፥1-19

**መግቢያ፡-** ይህ ክፍል እንደ ጌታ ፈቃድ ለመኖር ምሳሌያችን ክርስቶስ መሆኑንና ከቀድሞው እንደ ሥጋ ፍቃድ ከሆነ ኑሮ ስለመለየት ያስተምራል።

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እየኖረ መከራ በአማኝ ሕይወት ቢታይ እንደ እንግዳ ሊታይ አይገባም። ምክንያቱም በመጨረሻም ከጌታ የሆነ ፍርድ በሰው ሁሉ ላይ ይገለጻልና።

**ዓላማ፡-** በሕይወታችን በሚያልፍብን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን እያስከበርን ማለፍ እንዳለብን ለመገንዘብ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቁጥር 1-2
    - እንዴት ያለን ኑሮ እንዲኖሩ ነው የሚያሳስባቸው?
    - ለዚህ መሠረቱ ምንድን ነው?
    - በሥጋ መከራን የተቀበለ ኃጢያትን ትቶአል ሲል ምን ማለቱ ነው?
    - በሥጋ መከራን መቀበል ከኃጢያት ጋር እንዴት ይያያዛል?
2. ቁጥር 3-4 በመመልከት
    - ይበቃል የሚላቸው ስለምንድን ነው?
    - ስለምንድን ነው በውጪ ያሉት የሚገረሙት?
3. ቁጥር 5-6 በመመልከት
    - መልስ የሚሰጡት እነማን ናቸው?
    - ለማን መልስ ይሰጣሉ? ለምን ይፈረድባቸዋል?
    - የፍርዱ ውጤትስ?
    - በመንፈስ ግን እንደ እግዚአብሔር ይኖራሉ ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ቁጥር 7-9 በመመልከት
    - የነገር ሁሉ መጨረሻ ቀርቦአል የሚለው ምንን ያመለክታል?
    - ይህን አስመልክቶ የሚሰጣቸው ምክሮች ምን ምን ናቸው?
    - “እንደ ባለ አዕምሮ” እና “በመጠን ኑሩ” ሲል ምን ማለቱ ነው?
    - ስለፍቅር (መዋደድ) ምን ተጠቅሶአል? ምንስ ማለት ነው?
    - “የፍቅር ብዛት ኃጢያትን ይሸፍናል።” እንዴት?
5. ቁጥር 9-11 በመመልከት
    - እርስ በርስ ሊኖር ስለሚገባ አቀባበል ምን ይመክራል?

- እግዚአብሔርን የሚያመሰግንባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?
- ስለ ጸጋና አገልግሎት የተገለጠው ምንድን ነው?
- በቁጥር 11 የሚናገርና የሚያገለልግል ሊኖረው ስለሚገባ መረዳት ምን ተጠቅሶል? ውጤቱስ? በማን በኩል?

ለመረው፡- እንደ እግዚአብሔር ቃል፥ ከጌታ በሚሰጠው ኃይል።
ፍሬው ደግሞ በነገር ሁሉ ጌታ ይከብር ዘንድ።
መንገዱ ክብርና ስልጣን ባለው በክርስቶስ በኩል።

6. ቁጥር 12-14 በመመልከት (የሚመክራቸው)
    - በምን እንዲደነቁ ነው?
    - ይህንስ እንዴት ነው የገለጸው?
    - ከመደነቅ ይልቅ እንዲደሰቱ የሚያቀርብላቸው አሳቦች ምንድን ናቸው?
    - ስለ ጌታ የመነቀፋቸው ፍሬ ምንድን ነው?
7. በቁጥር 15-16 የተገለጡ ሁለት መከራዎች ምን ምን ናቸው? የቱን ነው እንዳያፍሩበት የተገለጸው? ለምን?
8. በቁጥር 17-18 በማነጻጸር የሚያስተላልፈው ሀሳብ ምንድን ነው? ምንስ ያመለክታል?
9. ቁጥር 19 እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራን የሚቀበሉ የተሰጧቸው ሁለት ምክር ምንድን ነው?

## ማዛመድ

1. ከምንባቡ ስለ ፀሎት ምን ተማርክ? ምንስ ወሰንክ?
2. ከክፍሉ እንደ ጌታ ፍቃድ እየተጓዝክ ሊገጥምህ ስለሚችል መከራ ልትረዳውና ልብ ልትል ስለሚገባህ ነገር ምን ተማርክ?
3. መደነቅ ስለሌለብህ ነገር ከክፍሉ ምን ተማርክ? ይልቅስ ምን ማድረግ እንዳለብህ ተረዳህ?
4. በመከራ ውስጥ ስናልፍ ምሳሌያችን ማነው? ለምንስ ይመስልሃል የተሰጠን?

የሚጠና ጥቅስ 1ኛ ጴጥ. 4፡6-8, 11

## ጥናት ዘጠኝ

## "መገዛት"

**1ጴጥ. 5፥1-14**

*መግቢያ፡-* በዛሬው ጥናታችን ውስጥ በቅዱሳን አንድነት ውስጥ በመሪነት ደረጃ ላሉ በትህትና ስለመገዛት እናጠናለን። በዚህ የመገዛት ህይወት ውስጥ የማይመችና ጥያቄ የሚፈጥርብን ነገር ቢኖርም በጊዜው ከፍ የሚያደርግ ጌታ መኖሩን በመረዳት መገዛት ፈውሳችን እንደሚሆን እንማራለን።

*ዓላማ፡-* ለሌሎች በትህትና መገዛት የጌታን ጸጋ መቀበያ መንገድ እንጂ መዋረድ አለመሆኑን ለማስገንዘብ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁጥር አንድ መሠረት ጴጥሮስ ራሱን ያቀረበው እንዴት ነው? የሚመክረውስ ማንን ነው?
2. በቁጥር 2-3
   - ሽማግሌዎቹን የሚያሳስባቸው ስለምንድን ነው?
   - ሽማግሌዎችን መንጋውን እንዴት እንዲጠብቁ ነው የሚመክራቸው?

   **ለመሪው፡-**
   - እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ እንዲጠብቁ
   - በግድ ሳይሆን፤ ረብን በመመኘት ሳይሆን ምሳሌ በመሆን
3. በቁጥር 4 መሠረት የሚገለጠው ማነው? የመገለጡ ውጤትስ?

   "የእረኞች አለቃ" ተብሎ መጠራቱ ምንን ያስገነዝባል?

4. በቁጥር 5
   - ለጐበዞች የተሰጣቸው ሁለት ምክሮች ምን ምን ናቸው?

     ለመሪው፡- ለሽማግሌዎች እንዲገዙ፤ ትህትናን እንዲለብሱ።
   - ስለምክሩ አስፈላጊነት የሚሰጠው ምክንያት ምንድን ነው?

     ለመሪው፡- እግዚአብሔር ትዕቢተኞችንን መጥላቱ፤ ለትሁታን ፀጋን መስጠቱ።
5. በቁጥር 6-7 ላይ
   - የተሰጠው ትዕዛዝ ምክር ምንድን ነው?
   - "ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች" የሚለው ሀረግ ምን ማለት ነው?
   - በቁጥር 6-7 ያለው ሀሳብ ከ1-5 ካለው ጋር እንዴት ይያያዛል?
6. በመጠን ኑሩ፥ ቁሙ፥ ንቁም የሚሉት ቃላት ምንን ይገልጻሉ? ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው?

7. በቀጥር 8-9 የሚሰጠው ምክርና ማስጠንቀቂያ ምንድን ናቸው? ለምን? እንዴት ትረዳዋለህ?
8. በቁጥር 9 መሠረት ዲያብሎስን በምን እንዲቃወሙ ነው የተሰጣቸው ምክር? ምንስ ምሳሌ ሰጣቸው?
9. በቁጥር 10-11 ስለመጠራታቸው ስለጠሪውና ስለእነሱ የተዘረዘረው ምንድን ነው?

   ለመሪው፡-
   - በክርስቶስ ወደ ዘላለም ክብሩ የተጠሩ
   - ጠሪው የጸጋ አምላክ ነው
   - መከራቸው ለጥቂት ጊዜ ነው
   - ጠሪው ፍጹም ያደርጋቸውል ያጸናቸዋል፤ ያበረታቸዋል።

10. በቁጥር 12-14 ስለጸጋ፤ ስለመልዕክተኛና ሰላምታን ስለሚልኩ የተዘረዘረውን ጥቀስ። ምንስ ያመለክታል?

    ለመሪው፡-
    - የሚቆምበት ፀጋ እውነተኛ የጌታ እንድትሆን
    - መልዕክቱን የአደረሰው የታመነው ስልዋኖስ
    - ሰላምታ ከባቢሎን ቤተ ክርስቲያንና ከማርቆስ
    - የፍቅር ሰላምታ ምክር

## ማዛመድ

1. ትዕቢተኛን እግዚአብሔር እንደሚቃወም በዚህ ክፍል ተመልክተናል። ስለዚህ ለመሪዎችና ስለመገዛት ምን ማድረግ ያለብህ ይመስልሃል?
2. ራስህን ስታስገዛ የማትረዳውና የሚያምህ ነገር እንኳን ቢያጋጥምህ ምን ማድረግ ያለብህ ይመስልሃል?
   * የሚያስጨንቅህን በእርሱ ላይ መጣል)
3. የእግዚአብሔር ጸጋ በሕይወትህ እንዲበዛ በምንባቡ መሠረት ምን ታደርጋለህ?

የሚጠና ጥቅስ 1ኛ ጴጥ. 5፥6-8

## ጥናት አሥር

### "የፍሬያማ ሕይወት ምሥጢር"
**2ኛ ጴጥ. 1፥1-15**

*መግቢያ፡-* ጴጥሮስ እግዚአብሔር ለቅዱሳን የሰጠውን ስጦታና

በተጨማሪ ቅዱሳኑ ሊያደርጉት ስለሚገባ ትጋት የጻፈውን እንመለከታለን።

*ዓላማ፡-* ሥራ ፈት፥ ፍሬ ቢስና የተሰናከለ ኑሮን ከመኖር ለመጠበቅ እግዚአብሔር የሰጠንን ስጦታ በትጋት መጠቀም እንዳለብን ለማስገንዘብ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ስለመልዕክቱ ጸሐፊና ተቀባዮች የተገለጸው ምንድን ነው?
   <u>ለመሪው</u>
   ስለ ጸሐፊው፡- የክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ
   ተቀባዮች፡- ጽድቅን ላገኙ፥ የከበረ እምነት ላላቸው
2. ከቁጥር 2-3 በመመልከት
   - እግዚአብሔር የሰጠው ምንድን ነው? ከምኑ የተነሳ?
   - ምንን በማወቃችን የተሰጠን ነው?
   - "ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል" ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - ይብዛላችሁ የሚላቸው ምንድን ነው? ከምን የተነሳ?

   <u>ለመሪው</u>
   1. ለሕይወትና ጌታን ለመምሰል የሚያስፈልግ ሁሉ ተሰጥቷል።
   2. ከክብሩና ከበጐነቱ የተነሳ
   3. መጥራቱን ለአወቁ
   4. አብና ወልድን ከማወቃቸው የተነሳ ፀጋና ሰላማቸው እንዲበዛ
3. በቁጥር 4
   - ከምን አምልጣችሁ ይላል?
   - ከምን ተካፋዮች እንድንሆን ጠራን?
   - ምን አይነት ተስፋ ነው የሰጠን?
   - የመለኮት ባህርይ ተካፋይ ሲል ምን ማለት ነው?
4. ከቁጥር 5-7 ምን እንዲያሳዩ (በምን እንዲተጉ ነው) የሚመክራቸው? ምን ማለት እንደሆነም በዝርዝር ተወያዩበት።
5. በቁጥር 8 የእነዚህ ነገሮች መብዛት የሚያስከትለው ፍሬ ምንድን ነው? "ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች" "አትሆኑም የሚለው ምን ያስረዳል?
6. ቁጥር 9 እነዚህ ነገሮች የሌሉት ሰው ባህርይ በእንዴት ነው የተገለጸው?
   <u>ለመሪው</u>

- ዕውር ነው።
- ከቅርብ ያለውን ብቻ ያያል። ከኃጢያት መንጻቱን ረስቶአል።

7. ቁጥር 10-11 በመመልከት
   - ስለምንድን ነው እንዲተጉ የሚያበረታታቸው? ምንስ ማለት ነው? ውጤቱስ?
   - በቁጥር 11 ላይ የተገለጸው ተስፋ ምንድን ነው? እንዴትስ ነው የተገለጸው?
8. ቁጥር 12-15 በመመልከት
   - ቸል አልልም የሚለው ስለምንድን ነው?
   - እስከ መቼ ነው ላነቃችሁ የሚገባኝ የሚለው?
   - ጌታ አመለከተኝ የሚለው ስለምንድን ነው?

## ማዛመድ

1. ከዛሬው ጥናት ፍሬ ቢስ እና ሥራ ፈት እንዳትሆን ማድረግ የሚገባህ ምንድን ነው?
2. እግዚአብሔር ሁሉን ሰጥቶናል፤ ግን ሁሉን በሥራ ላይ ለማዋል ከኛ ስለሚጠበቀው ከምንባቡ ምን ተማርክ? (ቁጥር 5-7)
3. ሰው በሕይወቱ መሰናክል ሲገጥመው እንዴት ሊወጣው እንደሚችል ከምንባቡ ምን ትማራለህ? ቁጥር 10
4. እግዚአብሔር ለሥጋዊ ሕይወትም ሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወት ሁሉን እንደሚሰጥህ ማወቅህ
   ሀ. ከምን ይጠብቅሃል?
   ለ. ምንስ እንድትፈጽም ያበረታታሃል?
5. ጴጥሮስ የሚጽፍላቸውን ለማነቃቃት የጸና ትጋት ያደርጋል። አንተስ ሌሎችን ለማበረታታት ለእንዴት ያለ እርምጃ ያነሳሳሃል?

የሚጠና ጥቅስ 2ኛ ጴጥ. 1፡5-7

## ጥናት አሥራ አንድ

### "የምታምነውን እወቅ"
### 2ኛ ጴጥ. 1፡16-21, 2፡1-10

**መግቢያ፡-** ጴጥሮስ ጌታን የተከተሉት ግርማውን አይተውና ይህም ያዩት በነቢያት የተነገረና የታመነ መሆኑን ይናገራል። በዚሁ ምንባብ እግዚአብሔር ኃጢአትን እንዴት አድርጎ እንደሚቀጣና ስለሀሰተኛ ነብያትና አስተማሪዎች ፍርድ ከብሉይ ኪዳን ምሳሌ በመጥቀስ የተናገረውን እንመለከታለን።

**ዓላማ፡-** ከስህተት ትምህርት ለመጠበቅ የተጻፈልንን የጌታን ቃል በሚገባ ማወቅ እንዳለብን ለማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁጥር 16 "አስታወቅናችሁ" በማለት የሚናገረው ስለማን ነው? እንዴትስ ነው ልምምዳቸውን የገለጠው?
2. ቁጥር 17- 18 የሚያነጻጽራቸው ሁለት ሁኔታዎች ምንና ምን ናቸው? ከገናናው ክብሩ የተባለለትና የተቀበለው ምንድን ነው? ይህን በየት ሳሉ ሰሙ? (ማር.9፡12)
3. ቁጥር 19
   - ከእርሱም ይልቅ በማለት የሚሰጠው ማስረጃ ምንድን ነው? ከየቱ ይልቅ?
   - እንዴት እንዲጠነቀቁለት ነው የሚነግራቸው?
   - ምን ሊያሳስባቸው ፈልጎ ይመስልሃል?
4. በቁጥር 20 እወቁ በማለት የሚሰጠው ማስጠንቀቅያ ምንድን ነው?
5. በቁጥር 21 ስለ ትንቢት አመጣጥ የሚያስገነዝበው ምንድን ነው?
6. የአየነውን (የተለማመድነውን) የሚለውን "እጅግ የጸና የትንቢት ቃል" ከሚለው መጽሐፍ ጋር ማስተያየት (ማነጻጸሩ) ምን ያስተምራል?
7. በ2፡1 ስለነማን ይናገራል? በየት አሉ? ስለሚያከናውኑትና ስለ ፍሬያቸው የተገለጠው ምንድን ነው?

   ለመሪው፡-

   የዋጃቸውን ይክዳሉ፤ ጥፋትን ያስባሉ፤ ኑፋቄን ያስገባሉ።
8. በቁጥር 2 ብዙዎች በምናቸው ይከተሏቸዋል? ከእነርሱ የተነሳ ምን ይሆናል? እንዴት?
9. በቁጥር 3 ስለነዚህ ሰዎች የተገለጠው ምንድን ነው?

   <u>ለመሪው</u>፡-

   የገንዘብ ምኞት/ ጥቅም/፥ ለፍርድና ለጥፋት የተጠበቁ
10. ቁጥር 4 - 10 በመመልከት
    - እግዚአብሔር አልራራላቸውም በማለት የሰጠው ምሳሌ ምንድን ነው? የተቀጡትስ በምንድን ነው?
    - በዐመፀኞች መካከል ስለዳኑት የተጠቀሰው ምንድን ነው?

- በቁጥር 9-10 የሚጠቅሳቸው ሁለት ሰዎች ባህርይና ስለ ፍጻሜያቸው የተሰጠውን ዝርዝር ተወያዩበት።

### ማዛመድ

1. የምትከተለው ተረት ሳይሆን እውነት እንደሆነ ከክፍሉ የተማርከው ምንድን ነው?
2. በዚህ ክፍል የሐሰት ትምህርት እንዴት ሰውን ሊወስድ እንደሚችል የተረዳህውን አካፍል።
3. እግዚአብሔር ስለምን  እንደማይራራ ከክፍሉ ተማርክ? ይሄስ ከምን መጠበቅ እንዳለብህ ያስተምርሃል?

የሚጠና ጥቅስ 2ኛ ጴጥ. 2፥9-10

## ጥናት አስራ ሁለት

## "ነጻነትህን ጠብቅ"
## 2ጴጥ. 2፥11-22

*መግቢያ፥-* ካለፈው ጥናታችን በመቀጠል ጴጥሮስ የሀሰተኛ አስተማሪዎች ባህርይና ድርጊት ምን እንደሆነና

መጨረሻቸውም እንዴት አሳዛኝ እንደሆነ የገለጸውን

እንመለከታለን።

*ዓላማ፥-* የተጠራነው ለነጻነት እንደሆነ አውቀን ከጠራን ጌታ በቀር የምንከተለውም ሆነ የምንሰማው ሊኖር እንደማይገባ ለማስገንዘብ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁጥር 11 ስለነማን ነው የሚናገረው? የተገለጠ ባህርያቸውስ? እንዴትና ከማን ጋርስ ነው የሚያነጻጽራቸው?
2. ቁጥር 12-14 በመመልከት
   - በቁጥር 12 ሀሰተኞችን እንዴት ነው የሚገልጣቸው?
   - በቁጥር 13-14 ስለዚህ ሕይወት ራሳቸውንና ሌሎችን አስመልክቶ የተጠቀሰውን ዝርዝር። ምንስ ያመለክታል?
3. ቁጥር 15-16 የሚጠቅሳቸውን ምንን የተዉና የተከተሉ ብሎ ነው የሚጠራቸው?
4. በቁጥር 17 ሰዎቹን የገለጸባቸው ምሳሌዎች ምንድን ናቸው? እያንዳንዱ ምንን እንደሚያሳይም ተነጋገርበት።
5. ቁጥር 18-19 በመመልከት
   - ማንን ነው የሚያሳስቱት?
   - የሚያሳስቱባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

   <u>ለመሪው</u>
   - በንግግራቸው፤ በሰው ፍላጎት (ድካም) በኩል በመቅረብ ያስታሉ።
   - በሰው መሻት ላይ የተመረኮዘ ባዶ ተስፋ በመስጠት።
   - የሚሰጧቸው ተስፋስ ምንድን ነው?
   - "ሰው ለተሸነፈበት ባሪያ ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. ቁጥር 20-23
   - ስለምን አይነት ሰዎች ይናገራል? በሕይወታቸው ስላለ ለውጥ ምን ይናገራል?
   - በምንስ ምሳሌ ይመስላቸዋል? ለምን?
   - የእንስሶቹ ባህርይ ከሰዎቹ ጋር እንዴት ነው የሚመሳሰለው?
   - በዚህ ክፍል የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

## ማዛመድ

1. ስለ ሀሳተኞች ባህርይና ፍጻሜ ከዚህ ክፍል ምን ትማራለህ? ለምንስ ያዘጋጅህል?
2. ከክፍሉ አዳዲሶችን ከሀሰተኞች ስለመጠበቅ ምን ትማራለህ?
3. በዚህ ክፍል ሥልጣንን መናቅ የምን ባህርይ እንደሆነ ተገነዘብህ?
4. ከተሰጡት ሁለት የእንስሳት ምሳሌዎች ስለሀሰተኞች ባህርይ ምን ተማርክ?

   በሚከተሉት አሳቦች ላይ አተኩር፡-
   - ሰው የጠላውን መልሶ ማድረግ ባህርይ አለውን?
   - ባርያስ ከመሆን የሚድንበት መንገድ ምን አለው?
   - በየግላችን ይህ ሕይወት እንዳይፈጸም ማድረግ ያለብህ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

የሚጠና ጥቅስ 2ኛ ጴጥ. 2፤20

## ጥናት አሥራ ሦስት

## "ተግቶ መጠበቅ"

## 2ኛ ጴጥ. 3፤1-18

**መግቢያ፡-** በኖኅ ዘመን ምድር በውኃ እንደጠፋች በመጨረሻም ዘመን ምድር ድንገተኛ የሆነ የጌታ ፍርድ ይጠብቃታል። ክርስቲያኖችም የጌታ ቀን እስኪመጣ ሊያከናውኑት ስለሚገባቸው ድርሻ የተጻፈውን እንመለከታለን።

**ዓላማ፡-** ጌታ ሰዎች እንዲድኑ እየታገሰ መሆኑን ተገንዝበን ዳግም እስኪመለስ ደስ የሚሰኝበትን ሕይወት መኖር እንዳለብን ለማስገንዘብ።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቁጥር 1-2 በመመልከት
   - እንዲያስታውሱ የሚፈልገው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?
   - በዚህ በሁለተኛው መልዕክት ምን አደርጋለሁ ይላቸዋል?
2. ቁጥር 3-4 በመመልከት
   - በመጨረሻው ዘመን ስለሚመጡ ሰዎች በምን ይለያሉ?
   - በምንስ ላይ ይዘብታሉ? ምንስ ይላሉ?
   - ከዘመናችን ጋር ምን ያህል ይመሳሰላል?
3. በቁጥር 5-7
   - እነዚህ ሰዎች ያላስተዋሉት እውነት ምንድን ነው?
   - ሰማይና ምድር የተጠበቁት እስከ ምን አይነት የፍርድ ቀን ነው?
   - እግዚአብሔር ይህችን ምድር በምንድን ነው የሚቀጣው?
4. ቁጥር 8-9 በመመልከት
   - ቀናትን አስመልክቶ የሚናገረው ሀሳብ ምንድን ነው? ምንስ ያመልክትሃል?
   - ጌታ የሚታገሰው ስለምንድን ነው?
   - ምን ማለት ነው ስለ እናንተ ይታገሳል ሲል?
5. በቁጥር 10
   - የጌታ ቀን የተገለጸው በምን ምሳሌ ነው?
   - እንደ ሌባ ሲል ምን ማለት ነው?
   - በጌታ ቀን የሚከሰተው እንዴት ነው የተገለጸው? ምንስ ያመለክትሃል?
6. ቁጥር 11-13 መሠረት
   - የፍጻሜውን ሁኔታ አስመልክቶ ምንድን ነው የሚመክራቸው?
   - እያስቸኰላችሁ (ቶሎ እንዲመጣ የምትሠሩ) ሲል ምን ማለት ነው?
   - የምንጠባበቀው ምንድን ነው?

7. ቁጥር 14-16
    - በምን ሁኔታ ነው እንዲጠባበቁ የሚመክራቸው?
    - "የጌታችንም መታገስ መዳናችሁ እንደሆነ ቁጠሩ" ሲል ምን ማለቱ ነው?
    - በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ሰውና ስለጻፈው መልዕክት ምንድን ነው የተጠቀሰው?
8. ቁጥር 17-18 ከምን እንዲጠነቀቁና በምን እዲያድጉ ነው የሚመክራቸው? በዝርዝር ተወያዩበት።
9. መልዕክቱን እንዴት ነው የሚቆጨው? ምንስ ያመለክታል?

## ማዛመድ

1. የጌታ መታገስ ለምን እንደሆነ ከምንባቡ ምን ተገነዘብክ?
2. የጌታ መታገስ ሰዎች እንዲድኑ መሆኑን ስትገነዘብ አንተ ልትወጣ የሚገባህ ድርሻ ምን እንደሆነ አስተዋልክ?
3. የጌታን ቀን እየተጠባበክ ሊኖርህ ስለሚገባ ትጋት የተማርከውን ለቡድንህ አካፍል።

የሚጠና ጥቅስ 2ኛ ጴጥ. 3፥8-9